# ምዕራፍ ፲፫ ገሙ ጐፋ ጕልበት ።

## መግለጫ ።

ከወርቁ በቀር ወለጋን የሚመስል ሀገር ነው። በሥራቸው የታወቁት ነገደ ኮንሶና ነገደ ዶርዜ የሚገኙት በዚህ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ነው ። በሐመር ባኮ በጐሬ ውስጥ ዎፍ አራሽ ቡና፣ ጥጥ፣ ሙዝ ሞልቷል ። ጥጡን ሳይዘሩት ስለሚበቅል ቂያ ይለቁበታል ብዙ መዋቶች አሉት ፤ ብረት በኰሬ ውስጥ ይወጣል ። የበረሃው አውሬ እንደ ኢሉ ባቦር ነው ። ሐይቆችም አባላን ፣ እስጢፋንያ ፣ ሩዶልፍ ናቸው ።

ወንዞች ማሴ በዞ ፣ ሎመቲ መነና ናቸው ።

ዋና ከተማው ፣ ጨንቻ ።

አውራጃዎች ፣ ሀ) ገሙ ጋርዱላ ፣ ለ) ሐመርና ባኮ ጎፋ ናቸው ።

ወሰን ፣ በሰሜንና በምዕራብ ከከፋ በደቡብ ከኬንያ በምሥራቅ ከሲዳሞ ይዋሰናል ።

፩) ልብ　　አንበሳና ነምር ዝሆንና ጐሽ
የምታድኚበት ከፋ ጕልበትሽ
ባለም ተደነቀ ተገረመልሽ ።
የኦሞን በረሃ የማሌን በረሃ የገሠገሥሽው
ጕልበትሽ ኀይለኛ ብርቱ ቢሆን ነው ።
ገሙ ጎፋ ጕልበት ተነሣ በዝና
ብልኮ በመሥራት በደን በግብርና ።
ጠላት አይደፍርሽም ብርታትሽ ከጠና
በጎፋ ጕልበትሽ ትመኪያለሽና ።
ይህ ገሙ ጕልበትሽ በጣም ዝነኛው
እንዲህ የበረታ ምን ብትበዪ ነው።

ኢትዮጵያ　　ሲሳይ ዘይንተረፍ በሐመር በኩሬ
ወዲያ ወዲህ ሳልል ከሠራሁ ጠንክሬ ።
በሐመር በባኮ በሰፊው ሜዳዬ
በጎፋ ጋርዱላ በገሙ ሻኃዬ
ይህ ዲካህ ማይባል የከብቱ መንጋዬ ።
ወይፈኑ ጊደሩ ላምና በሬው
ደቦሉ ወገዙ ጥጃው እምቦሳው
በወገን በወገን ይጥመለመላል
ባይን ግምት ነው እንጂ ማን ይቈጥረዋል ።
በሰፊው ሸኃዬ በቈላ ደጋው
በዐቀበት ቍልቍለት በእየማዘሪያው ።
ሲሰማራ ውሎ የጋርዱላ ከብቱ

ማታ መሰብሰቢያው ማሌ ነው በረቱ ።
ይህ ዲካህ ማይባል አልባለሁ ወተት
በሐመር በባኮ በኩሬ ግዛት ።
መንጋው ሚውልበት የከብቱ ሜዳው
የጋርዱላ ሜዳ ጥቁር ባሕር ነው ።
ከብቱም እንደ ሐይቁ ነጭና ጥቁር
አሻግሮ ለሚያየው ይመስላል ባሕር ።
በቈላው መሬቴ በእየበረሃው ፣
የሚረባው ፍየል ወሰንም የለው ።
ኮንሶ ያለው በጌ ቆመ ዐይኑን አፍጦ
መንቀሳወስ ቢያቅተው ላቱ ተገልብጦ ።
ባስፈለገኝ ጊዜ አንዳንዱን ሳርደው
ቀይ ሥጋ የሌለሽ ፍጹም ሞራ ነው ።
በመሎ በኮዛ መረዜ ሲያድግ
የሚወዳደረው አይገኝም በግ ።
የምበላው ሥጋ ምጠጣው ወተቴ
ወዲያ ወዲህ ሳልል ተኝቼ ከቤቴ ፣
ኃይልና ጤንነት ለመላ አከላቴ
ሊሰጠኝ ይችላል ብርታት ለጕልበቴ ።
፪ ሥጋና ወተቱን ለውቼ ለውቼ
አደን እሄዳለሁ ቀስቴን አነግቼ ።
መሣሪያዬን ይዤ ባጭሩ ታጥቄ
እገሠግሣለሁ ዘገሬን ነጥቄ
አድኜ ማመጣው የሥጋው እንስሳ
ውድድር የለውም ተወው አይነሣ ።
በሐመር በባኮ በጎፋ በዲሜ
ገድዬ እገባለሁ ደግሜ ደግሜ ።
በየኸው ብቅ ብለህ ሚዳቋና ሰሳ
ቡኸርና ኮርቄ የዱሩን እንስሳ
ድኩላው በርግጎ ከደኑ ሲነሣ
ሰባብሮ የሚጥል ይመስላል አንበሳ ።
ሳላና ውድንቢ ካዳኙም አይሸሽ
ዝነኛው ከርከሮ እንዳዚሁም ጐሽ ።
ላደን ብለን ወርደን በየበረሃው
የምናየው አውሬ አንጻርም የለው ።

አንበሳ ከነምር ዝሆን ከግስላ
ይመስላል ጓደኛ አንድነት ሲበላ ።
በእየሸንተረሩ አውራሪስ ቀጭኔ
የደጋ በግ መስሎ ሲሄድ አየሁ እኔ ።
በአሞ በረሃ እስከ እስጢፋንያ
የሚገኘው አውሬ የለውም አምሳያ ።
መንደር መንደር እንጂ ጦጣና ዝንጀሮ
በበረሃውማ ተምር መች ተዳፍሮ ።
ዱዳ የሚያደምቀው የጉሬዛው መንጋ
ከቄላ ሲመለስ ሲሄድ ወደ ደጋ
አቶ ነምርን ፈርቶ ዐየሁት ሲንጋጋ ።
ጉሬዛ በጽሕሙ እኔም በሸበቴ
እንከብር ነበር በደጋው በቤቴ ።
በጣም ባለጌ ነው ይኸስ በረሃው
ሽምግልና ያውቃል ያ ወይና ደጋው ።
እንዴት ያለ አገር ነው ሕግ የሌለበት
እርጅና አይከበር አይታይ ሽበት ።
አቊልቊላ እያየች ትላለች ጦጢት
በዚህ ጫካ ግና አዛዥ ጠፍቶበት
ጉረምሳው አንበሳ ያላንዳች ሥራት ።
አቶ ፋኖ ዝሆን በጕልበት በኀይል
ደኑን በረሃውን ያስገብረዋል ።
፫ ይህንን ቢሰማ ገመሩ ዝንጀሮ
የወይና ደጋውን ሥርዐት ተዘክሮ
በጣም አለቀሰ ዕድሉን አማሮ ።
በዚህ በበረሃው በበርካ መስኬቶ
ካቶ ነብር ጋራ አንበሳ ሸፍቶ
በሚኖርበቱ አራዊትን ገዝቶ
እኛን የሚያስታውስ ምን ድኃ ተገኝቶ ።
እያለ ሲያለቅስ ጉሬዛ ቢያየው
ቢበሳጭ አይሆንም ሰው ያለቦታው
ፍትሕንም አያገኝ ጊዜ ከልረዳው
አኳኋኑን ዐይቶ በጣም ሲከፋው
ሚረዳው ደጋፊ ወገን ከሌለው
ስለዚህ አታልቅስ ዝም በል አለው ።

ምክሩን ተቀብሎ አቶ ዝንጀሮም
ድምጡን አጠፋና ኖረ በሰላም ።
በሰማይ ሚበሩ ወፎች መናኸሪያ ፡
ወሰን የሌላቸው አራዊት መኖሪያ
ልጅ ተመልከተው ጫካና ዱሩን
የምኰራበትን የሀገሬን ደን ።
እኔን የሚያስደስት ወገን የሚያስመካ
ከሥር ሁኖ ሲያዩት ሰማይ የሚነካ
ወፍራምና ረጅም አለኝ ትልቅ ዋርካ ።
ጫፉ ቅርንጫፉ ሰማይ የሚደርስ
የደጋ ብልኮ የበረሃ ልብስ
ከላዩ ሲወጡ የሚያስመስል ወፍ
ያበቅላል መሬቴ ረጃጅም ዛፍ ።
በሲሳይም በኩል ለሰው የተስማማ
እንኮይና ዋንዛ አጋምና ዶቅማ
አልጣው ነው ምትል ከቀመስሽውማ ።
ይህን እበላና ወደ አደን ስሄድ
እገሠግሣለሁ በያዝሁት መንገድ ።
ወጥቼ ከሴማው ወግ ነጠቀኝና
በብዙ አወራሁኝ የበረሃ ዝና ።
አርሼ ዜፍሬ የማዘምረውን
እንውጣ ከዱሩ እንየው እህሌን ።
በእርሻዬ ጋርዱላ ማሳዬ ጉማይዴ
ባመት ሦስት ጊዜ አበቅላለሁ ስንዴ ።
አተር ከባቄላ ሌላውም እህል
በጎፋ ጉብሴ ዳዋ ይመስላል ።
፬ ሲዘራው በቆሎ ያስንቃል ሁሉን
የደጋውን ጫካ የቈላውን ደን ።
ብታየው በቈላው ማሽላዬንማ
ያልተመነጠረ ይመስልሃል ውድማ ።
አርሜ ኰትተቼ ምዘራው በውል
ይገኛል በኮንሶ ልዩ ልዩ እህል ።
ከቤቴ የሞላው ጤፍና ዳጉሳ
ቊጥሩም ትዝ አይለኝ ስሙም አይወሳ ።
ከብዙው አዝመራ ነገርሁህ ጥቂት

ከንቱ ላልጨርሰው ላውጋህ ስላትክልት ።
በሐመር በባኮ በኩሬ በማሌ
ወፍአራሹ አትክልቱ በጣሙን አያሌ ።
በእየዱሩ በቅሎ በቈላ ደጋው
በልቶም አልጨርሰው እንስሳና ሰው ።
ወፍ አራሹ ሙዜ ሲያፈራ ሲያምር
መሬት የተመቸው ይመስላል ዘተር ።
በዲሜ ሙሻራ በበርካ መስኬቶ
ዐውቆ በቀል አትክልት አያልቅም ተበልቶ ።
በየደኑ ያለው ሎሚ ብርቱካን
ያስንቃል ወተትን እንኳንስ እህሉን ።
ሥሩ ዘይንተረፍ በመሎዛ አገሬ
ድንችና ከባ በይናና ጐደሬ ።
ቅጠል ሥራ ሥሩን ከበላ ጉብል
የጫካውን ፍሬ ካገኘ ወደል
ምሳ ስጡኝ ብሎ መች ይጠይቃል ።
ፍሬውና አትክልቱ ሞልቶ በጫካው
ይሆነኛል ብሎ ማነው ሚዘራው ።
ወፍ አራሹ በቅሎ አትክልት ሲሆን ውድማ
ምን ይመስል ነበር ሰው ቢዘራውማ ።
ዝንጅብሉ ዱር ነው ጫካው ኮረሪማ
አለኝና መሬት ለሰብል የተስማማ ።
በባኮ በጎፋ ደግሞም በውብ ሐመር
ሰሚውን ይገርማል የቡናዩ ነገር ።
በመትከል በመዝራት ሰውን ሳያስቸግር
እሱ ዓውቆ ይበቅላል ዱሩ ሲመነጠር ።
በሁለተኛው ዓመት ይላል የምስራች
አፈራች አበበች ልጃችሁ ወለደች ።
ከዚያ በኋላማ ምኑ ቅጡ ታውቆ
ቢለቅሙት ቢለቅሙት አያልቅም ተዝቆ ።
ሲያፈራና ሲያብብ ቀርቦ ለሚያየው
ፍሬው ሎምባ ሾላ ዛፉ ግንድ ነው ።
፫ ወፍ አራሹ ቡና በየበረሃው
ረግፎ ይቀራል አጥቶ ሚለቅመው ።
በሐመር በባኮ ሎመቲ መነና

ሰውን አሰደደው ወፍ አራሹ ቡና ።
እንዲያው በልፍለፉ ምንም አይገባህ
ተደነቅ ተገረም አንድ ቀን መጥተህ ።
በኩሬ በማሌ ቢነሣኝ መንገድ
እለቅበታለሁ በጥጡ ስደድ ።
ተስቦ ተስቦ ሲይዝ መንገዱን
ሀገሩን ሲያለብሰው እየሆነ ደን
በሄት እኩል ሁኜ ልጠብቅ ከብቱን ።
ለከብቴ እንዲመቸው እንዲያምር ሻኃዬ
አቃጥለዋለሁ እሳት እፍ ብዬ ።
ምንም ባቃጥለው በሰደድ በቋያ
ከርሞ ዱር የሚሆን ይተካል ቡቃያ ።
ቄጥቀጫው መንጥሬ እኔስ ደከመኝ
ቁርጨው እንዳጠፋው መንግሥት ካልረዳኝ ።

ል ብ
ለምን ታጠፊያለሽ መልካሙን አዝመራ
የሚችልልሽን አብቦ ሲያፈራ ።
ያማረ ብልኮ ኩታም አበባው
ፍሬውም እንዲሁ የጾም ቅባት ነው ።

ኢትዮጵያ
ጫካ በረሃውን ደንና ዱሩን
ተራራ ሽንተረር አረሀ ሜዳውን
ጥጥ ፈልቶ ከያዘው መላ ሀገሩን
የምነዳው መንጋ ከብቴ ምን ይሁን ።
ስለዚህ አትወሽክት ያላወቅሽውን
መንጥሬ ቄጥቀጫው ቁርጨው ጥጡን
ከብቴን አረባለሁ ነኝና ዘላን ።

ል ብ
እማዬ አትቈጪ ሐሳብ ብነግርሽ
የሚጠቅምሽን ግን አንቺ ታውቂያለሽ ።

ኢትዮጵያ
ማታውቀውን ታሪክ ብዙውን ስነግርህ
አዎን አዎን እንጂ በጆሮ እየሰማህ
ዕዳ ትገባለህ አርማለሁ ብለህ ።

ል ብ
ይቅርታ አድርጊልኝ እማዬ ያሁኑን
ዝም ብዬ እሰማለሁ ለመጭውስ ቀን ።

ኢትዮጵያ
ጥጡን አቃጥዬ አትክልቱን መንጥሬ
ከብት አረባለሁኝ በማሌ በኩሬ ።
በገሙ ጋርዱላ በየባሕር ሽሹ

እንፈትላለን ብለው ልጆቹ ሲኳኹ
ጥጡን እያረሱ ሲዘሩት አመኹ ።

ጊ　　በጣሙን ነደደኝ በዚህ ሥራቸው
በገሙ ተከሉ ኩሬ ሳነደው ።
ላነደው አስቤ ተውሁት ራርቼ
በመጠን ከሆነ መጥቀሙን ዐይቼ ።

ልብ　　አሁንስ እማዬ መሰልሽ አውደልዳይ
እሳት እፍ ብለሽ የምታቃጥይ ።
ልጅሽ የዘራውን በእጅሽ የምትነቅይ
የሴቶችን ሙያ ጥጥ አትወጅም ወይ ?

ኢትዮጵያ　　ፈትልስ እወዳለሁ ባለሙያ ነኝ
በከንሶ በዶርዜ መጥተህ ባየኸኝ ።
በከብቱ ሻኅዬ ሳልዘራው ሲበቅል
በጣሙን ነደደኝ እኔ ምን ልበል ።
በገበያ ነጋዴ ከተቀለበለበ
የምትፈልገውን ዕቃ እያቀረበ
ግዛ ግዛ ብሎ ከተስገበገበ ።
ቅልብልብ መናቁ የታወቀ ነው
ትኰራበታለህ ምንም ብትወደው ።
የምትፈልገውን እንካ እንካ ቢልህ
ጥለህ ትሄዳለህ ሁሉንም ትተህ ።
ለዚሁ ማስረጃ ልቧ እየፈለገ
ሴት ወንድ ቢጠይቃት እግሯ አፈገፈገ ።
ባል እየፈለገች ልጃገረድም
እጮኛ ቢመጣ ስትሽኰረመም
ጊዜ ትወስዳለች ቶሎ እሺ አትልም ።
ዕለቱን ጠይቆ እሺ ብትልማ
የሚፈልገውን ዕለቱን ከሰማ
እንኳንስ ባልና አይሆንም ውሽማ ።
የአዳም ልጅ ከገና ሳይለፋ ጉልበቱ
የተሰበሰበው በመላ ንብረቱ
በከንቱ እንደ መጣ ይጠፋል በከንቱ ።
ስለዚህም ጥጤ በቅሎ ሳልዘራው
ሲያብብ ሲፈነዳ ቋያ እሳት በላው ።
በቀረው ቄላዬ ከብት ባልበዛበት

አርሜ ኰትኵቼ እኔው ተክልሁት ።
፯ ዱሩን እንተውና ወደቤት እንግባ
ንድፌ እንድታየው ሲመስል አበባ ።
አስተምሬ አለሁኝ ሙያ ጥበብን
የበኸር ልጆቼን ኮንሶና ዶርዜን ።
በኮንሶ ጋርዱላ በገሙ በጎፋ
ባየህልኝ ዶርዜን በጥበብ ሲለፋ ።
ምሽቱ እየፈተለች ኮንሶ ሚሠራው
ሰውን ያስጐመጃል ጥሩው ብልኮው ።
ብልኮውን ይዞ ገበያ ቢወጣ
መቶና ሰማንያ እንጫርሮልህ መጣ ።
የሚሠራበቱ ምንድር ነው ጥበቡ
የዶርዜ ብልኮ ሰፋፊ ነው አርቡ ።
ጥበቡን እያየ በመላው ዓለም ።
ይደንቃል ይገርማል የማይል የለም ።
ዋዕዩ ሲያቃጥለው ብርዱ ሲነጨው
ተርዞ ተራቁቶ ፍጥረት ሲጨንቀው
ጥበበኛው ልጄ ዶርዜ አለበሰው ።
ቀጭኑ ጥበቡ ዶርዜ የሠራው
አቻ ባልንጀራ አምሳያም የለው ።
በገሙ ገበያ በጋርዱላ ቤት
ቄጥረህ አትዘልቀውም የልብሱን ዐይነት
እንዲያው መታከት ነው ከንቱ መጃጃት ።
ኩታና ጥንግ ድርብ የሴቱ ቀሚስ
ዐይነቱ ይገርማል እንኳን ይለበስ ።
ቀሚሴን ለብሼ ኩታዬን ደርቤ
በጎፋ በገሙ ፈረስ እንደ ልቤ
ስጋልብ ባየኸኝ ሰንጋዬን ቀልቤ ።
በኮንሶ በገሙ በጎፋ ሰፈር
የሚሠራው ሸክላ እንደምን ያምር ።
ብረቱን አውጥቼ በዲሜ በኩሬ
በወናፍ ለይቼ አፈሩን ጠንክሬ
ማረሻና ወገል የበ መልካም ጨሬ
እሠራዋለሁኝ እጅግ አሳምሬ
ዝናዬ እንዲሰማ እንዲታወቅ ክብሬ ።

የሥራዬ ቍጥሩ እጅግ ብዙ ነው
ጐረፍ ጐረፍ አርገን ዐይተን ካልተውነው ።
ትወድ እንደሆነ ዋና መዋኘት
ተቈጥሮ የማያልቅ አለልህ ጅረት ።
በዐዞ በማዜ ሎመቲ መነና
ተኝተህም ብትውል ይሆንሃል ጤና ።

**፳ ልብ** እንደምን ደስ አለኝ እማዬ በጠና
ለኔ ጥቅም ብለሽ ብታነሺ ዋና ።

**ኢትዮጵያ** ከእነዚህም በላይ ዋና ከወደድህ
የማርጋሪታ ባሕር ሰፊው አለልህ ።
ገሙና ጋርዱላ በዙሪያው ያለው
ነጭ ጥቍር እያለ ከፋፍሎ ያዘው ።
ትላንትና ማታ ሲዳሞ ነበሩ
ዕያቸው ልጆቼን መጡ ተሻገሩ ።
እነዚያ ሲመጡ እነ‍ህ ተሳፈሩ
ሄዱ ገሠገሡ በጀልባ በረሩ ።
በእግዜር ድልድይም ላይ ያበላን ባሕር
እግረኛው ይታያል በእግሩ ሲሻገር ።
ታምር ነው ዕፁብ ነው የእግዚአብሔር ድልድይ
ነጭና ጥቍር አርጎ ባሕር የሚለይ ።

**ልብ** በጣሙን ገረመኝ ተዘርግቶ ሳይ
አዞና ጉማሬ ዓሣ አለበት ወይ ?

**ኢትዮጵያ** ሁሉም ከዚህ በላይ እንደ ጠየቅሽው
ዓሣና ጉማሬ ዘይንተረፍ ነው ።
ሊበላ ፈልጎ ልጄ ካሠገረ
ሞልቷል በእየወንዙ ዓሣ መች ቸገረ ።
በአሞ በማዜ በመንና በዐዞ
የሚገለብጠው አምባዛና ጐርዞ
ጠጠር የሚመስለው ታላላቁ ሰርዞ
በወጥመድ በመረብ አያልቅም ተይዞ ።
ወርጀም ካጠመድሁ ደግሞም በሩዶልፍ
በሺ ይቀርና አገኛለሁ በልፍ ።
ዓሣውን ለማሥገር በታንኳ ስሰፍ
መስዬ እታያለሁ የባሕር ላይ ወፍ ።
የሚወርደው ጅረት በእየተራራው

መሥፈርቱን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው ።
ሌላው ይቅርና በለምለሙ ገንታ
ይወጣል አርባ ምንጭ ሁሉም ካንድ ጉብታ ።
ተወት እናርግና ባሕርና ወንዙን
እስቲ እናነሣሣው መዋት ደበሉን ።
በጎፋ በረሃ የቢቦ መዋት
ፈንቅሎ ይወጣል አንድ ሜትር አለት ።
ፈልፍሎ ፈልፍሎ በመሮ ሠርሥሮ
መዋቴ ይወጣል ደንጊያውን ተርትሮ ።
በማሌ በረሃ ጥሩ መዋት አለ
ድሁር የማይቀርበው እጅጉን ከጋለ ።
ከሩቅ እየመጣ የሚፈሰው
በእነዚህ መዋቶቹ ቍጥርም የለው ።

<u>ልብ</u> ውበትሽን ሙያሽን እማዬ ሰማሁ
ፍቀጅልኝ ልሂድ እቸኵላለሁ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ፈቅጃልሃለሁ አሁን ከቸኰልህ
በብዙ እንዳወራህ ቶሎ ና እባክህ ።

<u>ልብ</u> ከብትሽ በጣም ብዙ አዝመራሽ ዱር ነው
ቈጥሮ ሚጨርሰው አይገኝም ሰው ።
ላደረግሽው ሁሉ መወድስ ሰጥቼ
ሥራና ግብርሽን በሰፊው አትቼ ።
እሄዳለሁ ዛሬ ለሰው ልናገር
በቶሎ መምጣቴም አይጠረጠር ።

## <u>መ ወ ድ ስ ።</u>

የበረሃ ጀግኖች ዝሆን ነብርና ግስላ
ካንበሳ ጋራ ኃያል የጦር መሪያቸው ሁነው ፤
የማደሪያ መሬት ደን ለጀግንነታቸው ጽፈው
ተቀበሉ ጎፋን ጉልበትሽን ስመው ፤
ንግሥት ኢትዮጵያ ፤
ለመኖሪያቸው ፈቅደሽ በፈርማ ብትሰጫቸው ።
ለነፍስም የሚያሠጋ ይህነን ዓለም ንቀው ፤
አይሆንምና ሕይወት ተድላ ዓለም ወይና ደጋው
ሰው ስለሌለም ከቅርብ በጣም ይዛናል ልባቸው
አራዊት ባሕታውያን በገሙ ጎፋ ማደሪያቸው ።

## ምዕራፍ ፲፬ አሩሲ እግርባት ።

### መ ግ ለ ጫ ።

ለእርሻና ለከብት ርቢ የተመቸ ነው ። ትግሬን ፤ ሸዋን ፤ አሩሲን የባዕድ ግዛት አያ ዋስናቸውም ። አብዛኛው ሕዝብ ዘላን ነው ። ዘላኖች ቅርጭጭት እንዳይዛቸው እግር ባታቸውን ቅቤ ስለሚቀቡ በዚሁ ተሰይሟል ።

ሐይቆች ዘዋይ ፤ ላንጋኖ ፤ ሻላ ፡ ናቸው ። ዱሩ መካከለኛ ነው ።

ዋና ከተማው አሰላ ይባላል ።

አውራጃዎች ፤ ሀ) አሰላ ፡ ለ) ጢቾ ፡ ሐ) ከምባታ ናቸው ።

ወሰን ፡ አሩሲን የሚያዋስኑት ጠቅላይ ግዛቶች በሰሜን ሸዋ ፡ በምዕራብ ከፋ ፡ በደ ቡብ ሲዳሞ ፤ በምሥራቅ ሐረርጌ ናቸው ።

ል ብ　　የደም ገንቦ ባትሽ የምትቆሚበት
አነሁሎ ፈጀው የዓለሙን ፍጥረት ።
የተደፋ ኮልባ አሩሲ ባትሽ
ዓለሙን ጠቀሰው ሰውን ጠራልሽ ።
እግርባትሽን ዐይቶ ያልተሰየ ሰው ፡
እንስሳ ነው እንጂ አእምሮም የለው ።
ጐረምሳ ጠላትሽ ስላየ ባትሽን
ምትገኚ መስሎት እንዲያው ባንድ ቀን
ሲከተልሽ ዋለ ኋላ ኋላሽን ።
ከጥንት የመጣ ነው ጥሩ እግር ባት ሲያይ
ሴትን መከተሉ ጐረምሳ አታላይ ።
ጐበዙ ይቅርና ከመንገድ ያየሽ
ባትሽን መች ጠገበው ዘመድ ወዳጅሽ ።
አጥበሽ በጥሩ ውኃ ወልውለሽ በአበሜ (ሽቱ)
ዛፍ ሹራብሽን ለብሰሽ ጫማሽን ልምላሜ ።
ገበያ ውድድር ብትወጭ አድርገሽ
እግር ባትሽን ዐይቶ ብልጫውን ሰጠሽ ።
አንዱ ባንዱ ሲስቅ ጀምበር ይጠልቃል
እንግዶች ቢያደንቁ ምን ያስደንቃል ።
ዐይተው የማያውቁት እንዳንች ያለች ሴት
እግርባተ መልካም ተረከዘ ክት
እኛ እንኳ ልጆችሽ አብረን ያለ ነው
ሁልጊዜ እያየን መቼ ጠገብነው ።
ሰዎቹ ሲያወሩ ስለግር ባትሽ

ዕፁብ ነው ግሩም ነው ውበቱ ሲሉሽ ።
አስተውዬ ባየው እኔም በቀደም
ተገረመ አንጎሌ ደነቀው ልቤም ።
እንዲህ አፈርጥሞ ያወለወለው
የተደፋ ኮልባ ወሊት ሚመስለው ።
ላስተዋለው ሁሉ ሁኖ በጽሙና
አንጎል አስደናቂ አነሁላይ ልቡና
ለሰው ቀልብ ተስማሚ ማራኪ ሕሊና ።
በመልክ በውበቱ የሰው ስሜት ሳቢ
ተስማምቶ ሚወደው የሁሉም ውቃቢ ።
ባለቡላ ሰንጋ በፈረስ ሳለሽ
ዓለም ያደነቀው አሻግሮ ሲያይሽ ።
እንዲያ ሲያተሰትስ ፈጥኖ ሲያኰበኩብ
ለጉግስም ወድድር ጬሌውን ሲጋልብ ።
ከጀርባው ቍጭ ብለሽ ስትገርፊው ባለንጋ
እጅጉን ሲያስደስት የፈረስሽ ሰንጋ ።
ዓለም ተገረመ እጅግ ተደነቀ
ባትሽ ስለታየው እያብረቀረቀ ።
ባለም ፍጥረት ዘንዳ የሚያስደንቅሽ
ክቱ ተረከዝሽ ደማሙ ባትሽ ።
እንደዚህ ያማረው ያንጸባረቀው
እማዬ ንገሪኝ ምን ብትበዪ ነው ።

ኢትዮጵያ የምጠጣው ቅቤ የሚያሳምር ኲማ
ስንቱ ይቈጠራል የምባለውማ ፡
ዝናውና ወሬው ባለም የተሰማ ።
ማርም አይቸግረኝ አለኝ ብዙ ጣዝማ ።
በየዱሩ ሳለ ቍጥር የለሽ አማጋ
ማሩን እውጣለሁ አንዳችም ሳልሠጋ
በየፈረፈሩ በቈላ ደጋዬ
ብዙ ሕዝብ ይሸኛል ማሩ የጣዝማዬ ።

ልብ አፌን ምራቅ ሞላው ንብሽና ጣዝማ
ጥሩ ማር መስጠቱን እማዬ ብስማ ።

ኢትዮጵያ እኔ ሳልፈቅድልህ ፍጆታ ሳልሰጥ
አድምጥ ዝም ብለህ ወጌን አታቋርጥ ።
አለኝ ብዙ ምግብ ሰው የሚያስጐመጅ

ልብ የሚያንገበግብ የሚያሰመጥጥ እጅ ።
ቀጭ ብለህ ካዳመጥህ ጀሮህን ከፍተህ
እነግርሃለሁኝ ሳለሁ እናትህ ።
በል እስቲ እንመለስ ወደ መሠረቱ
የማሩ ወጋችን እንዳይቀር በከንቱ ።
ቀፎዬን ስሰቅል ከረጅም ዕንጨት
የሚገባው ንቤ በጥቂት ሳምንት
ጉልቁ ይቅርና የለውም መስፈርት ።
ከሁለት ወር በኋላ ማሩ ሲሰናዳ
ንቤን አራግፌ ማሬን ባቆማዳ
ይገፍ እመለሳለሁ ልጋብዝ እንግዳ ።
ወዲያው እየሮጥሁ ስደርስ ከቤቴ
ብርዙን ስቸልሰው ይረካል ጥማቴ
ደግሞም በፍርንዱስ ይርሳል አንጀቴ ።
ንቤን አራግፌ ማሩን ከወሰድሁ
ቀፎዬን መልሼ እሰቅለዋለሁ ።
ንቧ ተመልሳ ትገባበትና
ትሠራልኛለች ማሩን እንደገና ።
ጣዝማዬም እንዲሁ በየፈረፈሩ
ሲፈላ ይገኛል ልጆቼ ሲዞሩ ።
ቤቴን እሄዳለሁ ዕቃዬ ሲሞላ
በእንሥራዬ ይገፍ ዲን የለሽ ወለላ ።
ምንም ሳልቀላቅል እንዳያው ለብቻው
ብግተው ለልጄ ልቡን የሚያመው
ጉልበቱ በረታ ጠፋ በሽታው ።

ልብ — አትቈጪ እናቴ ይሰጠኝ ፍጆታ ፥
ለቀፎ ለንብሽ ልናገር አንድ አፍታ ።
አራግፎ ከመፍጀት ከመጨፍጨፍማ
አትሠሪም ወይ ገንዳ ንብሽ እንዲለማ ።

ኢትዮጵያ — የንብ ቤት ሠርቼ ማር ሳይቸግረኝ
ከጓሮዬ ሁኖ ለምን ያዋክበኛል
ስወጣ ስገባ ለምን ይንደፈኝ ።
ስለዚህ ምን ቢሆን ሠርቼለት ገንዳ
በገዛ እጄ ስቤ አላመጣም ዕዳ ።
አሁንም ተወውና የገንዳውን ወሬ

ትንሽ እንጫወት ስላለኝ በርበሬ፣
ስዘራው ሜዳውን አርሼ ቆፍሬ
አንድ አረምም የለው ቃሪያው በሀገሬ ።
ድልሁን ስበላው በቅቤ በጨው
እንዴት ያል ምግብ ነው ሚተካከለው ።
ብትኑ ድልሁ አዋዜው ሲጥም
በጣም ይጣፍጣል ያላንዳች ቅመም ።
ባሩሲ ነገሌ ሚበቅለው በርበሬ
ሀብት ነው ለራሴ ኩራት ለሀገሬ ።
በነገሌ ወጭት በሮቢ ገበታ
መትቼ እበላለሁ የቅቤ ቁብታ ።
በጣም ተቀበለኝ ዓለም በደስታ
ተቀብቼ ቢያየኝ ራሴን ከምባታ ።
ባቴን እንዳይቄርጠው ክፉ ቅርጭጭት
እግሬን ተቀባሁት ርጎ ስልባቦት ።
የሮቢን ስልባቦት ማልዳ ከቀባሁ
ሳወለውል ውዬ እመለሳለሁ ።
እንኳንስ አካሌን ቄዳ ምቀባው
ባሩሲ ነገሌ ቅቤ ጭቃ ነው ።
ርጎውን ስገፋ ወተቱን ሳልበው
ግሬራው ሲሰፋ ሲታጠን ቋሚው
ደገኛው ተግባሬን መጥተህ ባየኸው ።
ሁጊጊዜ የማልባት ወተታም ጥገት
ባጀቱ ማትሆነው በጋና ክረምት
ሽለሙቋ ላሜ ምትገኝበት
አለኝ ብዙ መንጋ አለኝ ብዙ ከብት ።
ገዛሁ ብዙ መንጋ የበሬ የላም
ሻኸዬ ሳለልኝ ሚቸግር የለም ።
በጣም ዝነኛ ነው ያሩሲ ሰንጋው
በስባት በውፍረት ማነው የሚያክለው ።
ታላላቁ ሰንጋ መምጣቱ ሲሰማ
በአዲስ አበባ ላይ በሰፊው ከተማ
ዓለሙ ይርዳል ይጨነቃል ሰው
ደርሶ የሚወጋኝ እየመሰለው ።
በረጅም መጫኛ በብዙ ገመድ

ይሳባል ሰነጋዬ ባዲሱ መንገድ ።
ሰው ተሸበረ ሰማሁኝ ጫጫታ
ብቅ አለ በሬዬ ሁሉን እያምታታ ።
ዕየው ተሸበረ ከተማው ባንደፍታ
የታሠረበትን መጫኛ ቢፈታ ።
ወራሪ እንደገባ ጠላት እንደመጣ
ከተማው ፈረሰ ምስቅልቅሉ ወጣ ።
ጐረምሳው ራደ ሴቱ ተሸበረ
ደፍሮ የሚቀርበው አንድም አልነበረ ።
ሊይዝ ቢወላዳ ከጐበዞች አንዱ
በእግሩ ደቀደቀው መነሸው በቀንዱ ።
እንደ ዱር አራዊት እንደ ሽፍታ ሁል
ደግሞ እንደ ጃውሳ የሠራ ወንጀል
ፖሊስ ታዘዘበት በጥይት ሊገል ።
ጃውሳ ነውና የአሸበረ ሕዝብ
ጸጥታ ያጠፉ ያፈረሰ ዘብ
ሁኔታው ተሞላ በክብር መዝገብ ።
ዝነኛው ሰንጋዬ በማንም ሀገር
ካሩሲ ተነሥቶ ዓለም ሲያሸብር
በሥጋ እኔ እናትህ እንዴት ልቸገር !
በልቼ በልቼ ሆዴ ሲጠግብ
ለውጭ እሸጣለሁ እንኳን እኔ እራብ ።
በልቼ በልቼ የሰንጋዬን ጮማ
ወተቴን ጠጥቴ ከሆንሁኝ ጤናማ
ባቴ ካላማረ ካልወፈርሁኝማ ።
ይህች ሰው ዘለዓለም የምትሰለስል
ታማለች መሰለኝ ዓለሙ ይላል ።
ጮማዬን ቈርጬ ትኩሱን ወተት
ገልብጬ ብተኛ ሙሉውን ሌሊት ።
ወፈረልኝ ባቴ እግሬ ለሰለሰ
ልቡናዬ ረካ አንጐሌም ታደሰ ።
ሞት አይቀርምና እንካ ጉማ ሥጋ
ከስቡ በሬዬ ከታረደው ሰንጋ
በጣም ጤነኛ ነው ደዌም አያሠጋ ።
በልቼ ጠጥቼ ሆዴን ከሞላሁ

አመሰግናለሁ እጅ እየነሣሁ ።
በጣሙን ይገርማል ሰፌው ድግስሽ
ሲያዩት የሚያስጐመጅ ርጎና ጮማሽ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ሥጋውን ከበላህ ወተት ከጠጣህ
ካዝመራዬ ደግሞ ትንሽ ልንገርህ ።
ጤፌ ሲጐናዘል ዐይተህ ሻሼመኔ
ልታውቅ ትችላለህ ምን እንደሁ መጠኔ ።
ተርትሬ ገምሼ እንደ ተልባ ሁላ
ጤፍ እዘራዋለሁ ሜዳውን በሞላ
መሠለስም የለ እንኳንስ በሰላ ።

<u>ልብ</u> እመ አልተረዳኝም ያሁኑ ነገርሽ
ሳትጥሪ ሳትደግሚ ጤፍ እንዴት ዘራሽ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ጉብሱን ገምሼ ተርትሬ ጥጋቱን
ሰንጥቄ ማሳውን መንጥሬ ዱሩን ።
ሳልሠልስ ሳላበስል ምንም ሳልደክም
ደግሞም ሳልጐለጕል አረም ሳላርም ።
በላይ አለብስና ግምሻውን ዘርቼ
ሲለፉ እንደ ኖረ ገበሬ ኮርቼ
ማታ እመለሳለሁ በሬዬን ነድቼ ።
አንድ ጊዜ ከዘራሁ መሬት ከነካው
ማጭዴን አስዬ እስክጠይቀው
አረም አለ ብዬ ዙሬም አላየው ።
ከንሮ እንደሆነ እንዳይበላው ከብት
እጎበኘዋለሁ ቀንና ሌሊት ።
ሩቅ ከሆነ ግን የዘራሁበቱ
አንድ ጊዜ ሳላየው ያልፍና ወራቱ ።
ቍጭ ብዬ ዐስብና መከር መድረሱን
ዐይቼ ገምቼ መሸት መብሰሉን
የሌላውን እህል የጎረቤትን
እጠይቀዋለሁ ይገዥ ማጭዴን ።
ላየው ልጐበኘው ካፋፍ ብቅ ስል
ከመሬት ለጥ ብሎ እጅ ይነሣኛል ።
ባለሙ ታወቀ የጤፌ ትሕትና
አንገቱን ዘቅዝቆ እጅ ይነሣልና ።
ይህ ነው ምልክቱ ለፍሬያማ ሰው

ደፋ ለምበጥ ይላል ሲታየው ጌታው ።
ገብስና ማሽላ ስንዴና በቆሎ
እረ ምኑ ገዶ ባስላ ጭላሎ ።
በስመ ጥሩዎች ጢቾና ከንባታ
አለኝ ብዙ አዝመራ ሀገር የሚፈታ ።
አሁን የት ይገኛል አሩሲን ሚያህል
በከብት ርቢና ባዝመራ በእህል ።
የሚበቅለው ጥጤ ባሩሲ ነገሌ
ገበያ እየወጣ ይሸጣል በያሌ ።
ጫካውን ስዘራው ትንሽ ጨጫጭሬ
ከመንፈቅ በኋላ ይመስላል ጉፈሬ ።
አለኝ ብዙ ቡና ባሳውስ ማን ጫካ
የሚጣፍጥ ሸንኮር ልብን የሚያረካ ።
ሙዝዬንና ድንች ሌላውም አትክልት
ስዘራው ባየኸኝ ሁሉን በትጋት ።
ወረረው ዓለሙን አልተገኘም በታ
ቤተ ሰብእ የሚችል እንሰት በከንባታ ።

**ልብ** ስለ ከብት አወጋን ቅዱስና ርኵስ
ለእህልም እንዲሁ ማሽላና ገብስ
ምን ዛፍ ታገኛለሽ ከዕንጨት በኩልስ ።

**ኢትዮጵያ** አለኝ ይበቃኛል በዛፍ በኵልም
ለሰውም ባላውስ አልበደርም ።
አልፎ አልፎ ይገኛል ቀረሮና ሰምበ
ቅርንጫፉ ሰፍቶ ጥላው ተንዘርበ ።
አጋምና ግራር ውልክፋ ቀላበ
ምሳናና አሉማ ማብሰያ ለዳበ ።
በአሩሲ ነገሌ ቅርቃኅና ጽድ
የሸርሸር በታ ይመስላል ዐጸድ ።
ገተምና ቀረጥ አዛምራ አምጃ
ትዝ ያለኝን ጠራሁ የቀረውን እንጃ ።
ዛፉ ይበቃሃል በትቂት ካየህ
ና እንውጣ ከዱሩ ዘዋይ ልውስድህ ።
እግረ መንገዳችን ላንጋኖና ሻላ
ዙረህ እንድታየው ዓሣውን በሞላ ።
አጥማጅ ስለ ሌለ ደግሞውንም ዐሥጋሪ

መቃጥን የሚጥል በብርብር አስካሪ
በቀፎ ጋፋፊ ሰፊ መረብ ሠሪ ።
ዓሣው ዱለት መቶ አንድነት በሴራ
እስከ ዳር ይመጣል ማንንም ሳይፈራ ።
ጥቡልቅ ጥቡልቅ ይላል ዕየው ራቅ ብሎ
አምባዛና ጐምዠ የወፍጮ መጅ መስሎ ።
እጅግ ዘይንተረፍ የሰው ልጅ ሲሳይ
ላንጋኖና ሻላ ዘዋይ ለዘዋይ ።
ዓሣዬን በልቼ ከተሰማኝ ኃይል
በረሃ እወርዳለሁ ዝሆን ልገድል ።
አራዊቱን ሁሉ ልገድለው ሳንጫጫ
በመሣሪያ አይደለም በጥፊ በርግጫ ።

**ልብ** የውኃ መዋኛሽን አዝመራሽንም
ዐየሁት እየዞርሁ የቀረ የለም ።
እጅግ ያስደስታል ይሰያል ልቡና
ይዞ ስለሚገኝ ለሰው ሙሉ ጤና ።
ሁሉን እንዳየነ አዝመራና ከብት
እባክሽ አሳይኝ ደግሞ ትምህርት ቤት ።

**ኢትዮጵያ** ሁሉንም የያዘ አቅዱ የተስማማ
አለኝ በያውራጃው የትምህርት ቤትማ ።
ዓለም ያደነቀው ዝናው የተሰማ
አለኝ ራስ ዳርጌ ባሰላ ከተማ ።
ድንቍርና ጠላት በጣም ሚፈራው
ሥልጣኔ ጀብዱን በኃይል የሠራው
ታላቁ ራሳችን ራስ ዳርጌ ነው ።
በታላቁ መስፍን በራስ ዳርጌ ግቢ
ይመስላል አበባው በሚዝያ ወር ጥቢ ።
ነጭላና ቀ፦ንን ጽጌ ረዳ አበባ
ጮብዬ ጠምበለል የጐሎ ኮኰባ ።
እጅግ ተንዠርፍፎ ለምለሞ ያለው
ዓለምን ያስንቃል ገብተህ ብታየው ።
ከዚያም እልፍ ብሎ ከከተማው ዳር
ይገኛል ስዊድን የወንጌል መምህር ።
ሰብስቦ ይግታል ብዙ ሕፃናት
የልጅ ማሳደጊያ ትምህትን ወተት

ሌት ተቀን ጠንክሮ ያላንዳች ዕረፍት ።
ከብክበ ተጨንቆ ካሳደጋቸው
ሕፃናቱ ሁሉ ልጆቼ ናቸው ።
አንደኛ ደረጃ በመልካም ሥርዓት
ጨርሰው ሲወጡ በስምንት ዓመት
ለፍቶ ወጥቶ ወርዶ ላሳደጋቸው
ሕፃናቱ ሁሉ ልጨኛ ናቸው ።
ተዘዋውረህ ዕየው በመላ ክፍሉን
የትምህርት መስጫውን ማደሪያ ቤቱን ።

ልብ — እየዞርሁ ዓየሁት እንዴት ደስ ይላል
ተማሪ ለኑሮው ሁሉን ያገኛል ።
አቀማመጡ ነው የሚገርመው ደሞ
ዘዋይና ሻላ ይታያል ሲዳሞ ።
ልቡና ሚማርክ በሰፊው ሕንፃው
እማዬ ንግረኝ ይህስ ምንድር ነው ።
በዚሁ እንረዳው ርቀን ሳንሄድ
ኋላ እንዳልሳመለስ ያለውድ በግድ ።

ኢትዮጵያ — ከጠየቅሽኝማ ሆስፒታሉ ነው
የስዊንድን ማኅበር ድሮ የሠራው ።
ድውይ የሚፈውስ የሚያድን ሕመም
ተፈሪ መኰንን ይባላል ስሙም ።
ተፈሪ መኰንን አሰላን ከገዛ
ወባ አገር ለቀቀች በስሙ ተናዛ ።
ያ መጥፎ ጃውሳ ሰውን የገደለ
የቄላ ቍስልም ነፍሴን አውጭኝ አለ ።
ሄደ ገሠገሠ ጫካ ጫካውን
ተፈጥሞ ለቆ መንደር ዱዳውን ።
ተፈሪ መኰንን ሕዝቡን ከገዛው
ዓለም ተደሰተ ኖረ በጤናው ።
በሱ ተመከነ አገኘነ ተስፋ
ሐሴታችን በዝቶ ደስታችን ሰፋ
ሰዎችን የፈጀ ሕመም ጠላት ጠፋ ።
ሕመምተኛው ሁሉ ከደጃፍ ሲደርስ
ሕመሙ ይጠፋል ይሰጠዋል ፈውስ ።
ችግረኛ ድኃ ድንገት ሲታመም

ያለ ምንም ዋጋ ነው የሚታከም ።
ሕመሙ እንዳለፈ መዳን ሲጀምር
የመንፈስ ስጦታ ሃይማኖት ምግባር
ይዞ ይቀርበዋል የወንጌል መምህር ።
እንደዚህ አድርጎ ታክሞ ከወጣ
እንኳን ቂጥኝና አይፈራም ፈንጣጣ ።
እላለሁ ሁልጊዜ የተፈሪ አባት
መኰንን ስዊድን ይግባልኝ ገነት ።

ልብ
እማዬ ገረመኝ ሆስፒታሉን ባይ
ደግሞ ትምህርት ቤቱን ወገን የማይለይ ።
እንዲህ ያለ ሥራ በሰው አገር ላይ
ሃይማኖት ለመስበክ ለማከም ድውይ
ርቆ እየሄዱ ይደረጋል ወይ ።

ኢትዮጵያ
ትምህርት ቤት ያቆመ ሁሉንም የቻለ
ውረድ ሻሼመኔ ደግ ሚሲዮን አለ ።
ድውይ ይፈወሳል በቤቱ ጽዳት
ገና ሲያሰናዳ ሐኪም መድኃኒት ።
በእነሆ ሐኪም ቤቶች ሁኖ መድኃኒቴ
እግሬ ሲለመልም ወፈረልኝ ባቴ ።
የባቴን ታሪኩን የተረከዜን
በሙሉ እንኳ ባይሆን ባጭሩ አወጋን
ሴማችን ይለወጥ እስከ ዚህ ይብቃን ።

ልብ
ባወራሽኝ ታሪክ ስለተደሰትሁ
መወድስ ሰጥቸሽ እመ እሄዳለሁ ።

## መ ወ ድ ስ ።

ባረማመዷ ቅጠል እጅግ ተደነቀ
የሚያመዛዝን ሁሉን የገነት ውበት ጐረምሳ
አሻግሮ ቢያያት ከሩቅ ልምላሜ ቀሚሷን ለብሳ
ደግሞም በረጃጅም ዛፍ ራስዋን ከብሳ ።
ስትወርድም እግር ባቷን
ቅቤ ወልውላ ዘዋይ ጋፋ ለማምጣት ዓሣ ።
ባትዋምሂ እንዲታይላት ከሰው መካከል ደርሳ
ደርባ የደን ኩታ በቀሚሷ ላይ ስትነሣ
እየተንደደች ስትሄድ እንደ በረሃው አንበሳ
የልጃ ገረድ ኢትዮጵያ ውበቷ ስለሚያሳሳ ።

## ምዕራፍ ፲፬ ወሎ መልክዐ ።

### መግለጫ ።

የእህልና የፈረስ ሀገር ነው ። በወይና ደጋው ያለው ሰው መልከ መልካም ከመሆኑም በላይ ዘፈን ያውቃል ። በተለይ ዋድላ ደላንታ የሚባለው አውራጃ እንደ ጐጃም የሊቃውንት መፈጠሪያ የሊቅ መመንጫ ነው ።

በድሮ ዘመን የቅኔ ምስክር የነበሩት ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ናቸው ። ጥበበኞች መሆናቸውም በግልጽ የታወቀ ነው ።

የዋድላ ስለምንና ቅኔ ሳያቋርጥ ዘለዓለም ይወርዳል ።

ወንዞች በርከና ፤ ተከዜ ፤ በሽሎ ፤ ጂጣ ናቸው ።

ዋና ከተማው ደሴ ይባላል ።

ወሰን ፡ በሰሜን ትግሬ ፤ በምዕራብ በጌምድርና ጐጃም ፤ በደቡብ ሐረርጌና ሸዋ ፤ በምሥራቅ ሱማሌና ኤርትራ ያዋስኑታል ።

ወሎ ስምንት አውራጃዎች አሉት ፡ ሀ) ሐይቅ ፡ ለ) ዋግ ፡ ሐ) ላስታ ፡ መ) የጁ ፡ ሠ) አውሳ ፡ ረ) ኰምቦልሻ ፡ ሰ) ወረይሉ ፡ ቀ) ተንታ ናቸው ።

ልብ

የምታጌጭበት ገጽሽ ምድረ ወሎ
ዓለሙን ማረከው ቢታይ አወልውሎ ።
ገጽሽ የሚያበራው እንደ አጥቢያ ኰከብ
ሕሊና ያጠፋል ይማርካል ልብ ።
ገጽሽ ያጥቢያ ጮራ የሚያብረቀርቀው
ትክ ብሎ ለማየት ዓለሙን ጨነቀው ።
የፊትሽን ፈገግታ ወዝና ላህይ
ሰው ሁሉ ፈዘዘ አስተውሎ ሲያይ ።
እንዲህ ያለ ውበት እንዲህ ያለ ግርማ
እረ ምን በልተሽ ነው ያገኘሽ እማማ ።
እባክሽ ንገሪኝ ልንገረው ለሰው
ምስጢርሽ ላልገባው ለተጨነቀው ።
እኔም ጨነቀኝ በጣም ጠበበኝ
መልክሽ ሁል ጊዜ አዲስ እየሆነብኝ ።
ዳውንት ላይ ሁኜ ባየው መልክሽን
ፍጹም መስሎ ታየኝ ጣልያ ብራይን ።
የጣልያ ብራይን አንች ባንደበትሽ
ነግረሽኝ ነበረ ሁሉን ፈትተሽ ።
የሰማሁትን ሁሉ ከዚህ ፊት በዝና
ይኸው አየሁልሽ ዋድላ ደረስሁና ።

የጁ ሁኖ ሲያዩት ደግሞም መርጦ ላይ
በጣም ያስጐመጃል የገጽሽ ላህይ ።

**ኢትዮጵያ** አንተው ከጠየቅኸኝ የምበላውን
በል አድምጥ እንግዲህ ከፍተህ ጆሮህን ።
አየሬ ጤናማ እህሌ አለው ጠመቅ
ሲሳየ ብዙ ነው ተቈጥሮም አያልቅ ።
በዋድላ ደላንታ በሰፊው ሜዳዬ
አረባለሁ በጐች እንደ ልቡናዬ ።
በወሎ በኮረም ደግሞውንም በዋግ
ያለወግ ይረባል ፍየልና በግ ።
በላስታና በአገው በቆቦ ሲንጋጋ
ላየው ያስገርማል የፍየሉ መንጋ ።
አንድ እናት ቢገዙ ዘረ መልካሟን
ትፈለፍላለች መንታ መንታውን ።
ባመት ሁለት ጊዜ ከወለደች መንታ
ቤቱን ትሞላለች አንዲቱ ተንሻሽታ ።
ሽለሙቅ ከሆነች ከበላች አፈንቆ
ጨው በደንብ ካላሷት ወራቱን ጠብቆ
እንኳን ቁጥሯንና መንጋውን ማን ዐውቆ ።
ሙክቱን በልቼ ኰርቤሶቹን ሳይ
ፊቴ በጣም ያምራል ይመስላል ፀሐይ ።
ደግሞም ከዚህ በላይ የሚያስደስተኝ
ስመ ጥሩው በዓለም የአዳል በግ አለኝ ።
በዋድላ ያለው በግ እንደ ንብ ሲተም
ካፋፍ ላስተዋለው እንደምን ይገርም ።
የራያውን ርኀ ያዳልን ወተት
ጠጥቼ በልቼ ብታየው ድንገት
መልኬን አደነቀው ዋድላና ዳውንት ።
ወረይሉና ተንታ አማራ ሳይንት
በጣም አደነቁ ያለኝን ውበት ።

**ልብ** ከዚህ መልክሽ ጋራ በፈረስ ቢያይሽ
ዓለም ተጨነቀ ተገረመብሽ ።
ከውበትሽ በላይ የፈረስ ግልቢያሽ
በጣሙን ይገርማል ለሚያስተውልሽ ።
ወሎ ቢዝገመገም የፈረስሽ ድምጡ

ዋድላ ደላንታ ላይ በጎች ደነገጡ
በአዳልም በረኻ ጥጆች ፈረጠጡ ።
ፍየል በረገገ በላስታ በአገው
መንጋውም ጐፍቶ በራያ ያለው
በረት ሰብሮ ወጥቶ አንድም ሳይቀረው
የአዘቦን ማሽላ ውድማ አደረገው ።
ፈረስሽ አሽካክቶ ባነሣው ሁከት
ባደረገው ጣጣ በመጣው ጥፋት
ከብቱ ሁሉ ጠፍቶ ቢሄድ ጨፋ ሜዳ
አውሳ ወንድማችን በጣሙን ተጐዳ
ጨገሬታ አጣ አሉ ደግሞም ዋጠው ዕዳ ።
ከብቱ ይቅርና የቤት እንስሳው
ከደመ ነፍስ በቀር ዕውቀት የሌለው
ፈረስሽ ሲያሽካካ ሲፎግር ኮቲው
ካፋፉ ላይ ሁኖ ድንገት ቢሰማው
ዓለም ተቸገረ ደነገጠ ሰው ።
ተሸብሮ አደረ አማራ ሳይንት
ዋድላና ደላንታ በሙሉ መቄት
አገውና ላስታ የጁና ዳውንት
ዳናውን ቢሰማ ጦር መጣ መስሎት ።
ከምቦልሻና ተንታ ደግሞም ወረይሉ
ሲጨነቅ አደረ ሌሊቱን በሙሉ ።
አዳልና ራያ አመጠኛው ጀግና
ሁሉንም ታዘበው ጒድኳዱን ያዘና ።
በዚህ ሽብር ጊዜ የጠፋውን ሰው
እኔ ምን ዐውቄ ቤቱ ይቊጠረው ።
ፈረስሽ ተጋጡ አምልጦ ቢወጣ
እግሩን ሊጨብጠው ጀግናው አዳል መጣ ።
በጦርነት ሜዳ ሰንጋሽ ቢፋንን
ሲላው አዳል በርሮ ያዘው ጋማውን ።
በዚህ ፈረስ ሁነሽ በዋድላው ሜዳሽ
አንች እየነዳሽው ሲራመስ በግሽ
በላስታ በረኻ ደግሞም በዋግ ቄላ
ፍየልሽ ከዱሩ እንደ አሸን ሲፈላ
በራያ በአዘቦ በአዳል በዞብል

ከብትሽ በሸንው ላይ ተሰማርቶ ሳል
አሻግሮ ለሚያየው ሕልም ይመስለዋል ።
በጣም የሚገርመው ከዚህ ሁል በላይ
ፈረስ ግልቢያሽና የመልክሽ ላህይ ።
ከወተት ከሥጋ ሌላ ምን በላሽ
እንደዚህ ያማረ የቀላ ፊትሽ ፧

ኢትዮጵያ ሁሉንም ለማወቅ ከጠየቅኸኝስ
ብዙ ሲሳይ አለኝ ተርፎ የሚፈስ
ይመስላል ዓሣዬ የክረምት ደመና
ወርደህ ተመልከተው በሐይቅ በቡርከና ።
ብግፈው ብግፈው ብፈለፍለው
የበቆሎው ምርቴ ማለቂያም የለው ።
በጨፋ ቦርከና ጭው ባለ ሜዳው
በቆሎ ማሽላ ዛንገዳ አገዳው
የጨበና የጥድ ይመስላል ውጋግራ
ምሰሶ የሚሆን ቤትም የሚያሠራ ።
መከመሪያ ቢያጣ ቦታው ቢጠበው
በእየሸናው ቄርጦ ልጇ ከመረው ።
የጨፋ ቦርከና ጫካው ትዝ አለኝ
ልሂድ ተነሥቼ እስቲ ልቀቀኝ ።
መንጋውን ላሳይህ አሸንጌ እንውረድ
ሀብቴን ከብቴን ዓይተህ እንድትለው ጉድ ።
ባሸንጌ አካባቢ በሐይቅ በዙሪያው
በጨፋ ቦርከና በለምለም ሜዳው
የከብቱ መንጋዬ ጉንዳን ሚመስለው
እንኳን ቊጥርና መስፈርትም የለው ።

ልብ አሸንጌና ሐይቅን ጨፋንም ዐየሁ
ዘላን ነሽ ገበሬ እመ ተቸገርሁ ።

ኢትዮጵያ ገበሬና ዘላን ሁሉንም ብትል
አያሳፍርህም የእናትህ ባህል ፧
ላም አለኝ አልባለሁ በሬ አለኝ አርሳለሁ
ስለዚህ በሁለቱም እመሰገናለሁ ።
መች ይህን ብቻ ነው እኔ የምበላ
የዳውንትን ስንዴ የየጁን ማሽላ
የዋድላን ወለም የቆበን በቆሎ

የባቄላን ንፍሮ የጠመጁን ቈሎ
አቅርቤ እዝቃለሁ በላዳኤ ወሎ ።
ጠጁ የሚጣፍጥ የአማረ ሽታው
ያማጋ ማር አለኝ በአምባሰል በአገው ።
ወለላውን ውጩ ፍርንዱስ ሲመጣ
ብርዝን አልመኝም አምሮቴ ከወጣ ።
ሰቆጣና ዐምደ ወርቅ ተላጌ ጋዝጊብላ
ለድብና <u>ወላህ</u> ደግሞውንም ጥላላ
ወተቱን ጠጥቼ ነጭ ጤፍን ብበላ
ወዝ ቅቤው ቀለጠ እንደ ማር ወለላ ።
ከነዚህ አገሮች ሚዘመረው ሰብል
ራሴን አጥግቦ ለሰው ይተርፋል ።
<u>ተደቡኜ</u> አድሬ በዋድላ ዝተት
ከቤቴ ስወጣ ማለዳ ጥዷት
ወዜ ሲያሸበርቅ እንደ ከዋክብት
በማድነቅ መነጠር አሻግሮ ቢያየው
የዚህን ዓለም ሰው በጣም ገረመው ።

<u>ል ብ</u>　　እውነትሽ እናቴ ከዚህ መልስሽ ጋራ
በራያ በረኻ በአምባሰል ተራራ
በማለዳ ወጥቶ ከብትሽ ሲሰማራ
እያየሽ ይውላል ዓለም በዚህ ጐራ
ጠላትሽ ሲተክዝ ወዳጅሽ ሲኰራ ።
በፈረስሽ ሁነሽ ስትንጐራጐሪ
ድምጥሽን ሰምቼ አንድ ቀን ከዳሪ
በሩቁ ሳዳምጥ ዘፈን ነው መሰሎኝ
ስለምን ምርምር ቅኔ ሆነብኝ
ዝተትሽን ለብሰሽ የምታወርጅው
የዋድላ ጐዳና ለካስ ቅኔ ነው ።
ከዚያ ከሰማሁት ካማረው ቅኔሽ
ከሴቱ ስለምን ከጥሩው ግጥምሽ
ካርሖ ጭፋሮና ካምባሰል ዘፈን
ንገሪኝ እናቴ አማረኝ እኔን ።

<u>ኢትዮጵያ</u>　　አንተን ካስደሰተህ ከከጀለህማ
አወርድልሃለሁ ቊጭ በልና ስማ ።
ስናደድ ስበሳጭ ኀዘን ሲገባኝ

አንጐራጐራለሁ እንዲህ እያልሁኝ
የጁስ ላስታ ለምኔ
አረ ! ተዋድላ ለኔ ።
የበጌምድር መንገድ
በላስታ ነበር የሚያስሄድ
ለምን ታደክመኛለህ ፤
በደላንታ አዙረህ ።
ዋድላ ደላንታ ዳውንት
እምብዛ በጉን አርብቶት
አልሰበ አላሉ ቢያርዱት
እንደኛ አገር ጠቦት ።

ያፄ ዮሐንስ ባለሟል ብርሌ ሰይፉ የሚባሉ ዐይነ ሥውር ተከተለኝ
እየተባሉ በመዘር ብዙ ድካም ስለደረሰባቸው የገጠሙት ግጥም ።

ዕንቅፋቱም ይምታህ እሾሁም ይውጋህ
እኔውም ለልኬ ጫማ አልገዛልህ
አንተ እግሬ አንተ እግሬ ምን ታዞረኛለህ ።

አንድ ወታደር የገበሬውን ምሽት መጫኑ ባሰ ባልሽ እያለ
አታሎ ስለወሰደበት ገበሬው ያንጐራጐረው ፤

ወታደር ያግባሽ እንዳወቀ
እኔስ ወረቴ አለቀ ።

ወታደርም ማታ በሉ መሰለኝ ብሎ ሂዶ የራሱን መቀነን በልቶ መጥቶ
ጠሚን ስላሳደራት ሴትዮዋ የሚከተለውን ገጥማ ወደ ባልዋ ተመለሰች።

የመጫኑን ነገር ስታጫውተኝ
አንተም ሰው አይደለህ በሉ መሰለኝ

በዐፄ ዮሐንስ ጊዜ አንድ እስላም አምኖ ፡ ክዶ ስለሞተ
ጐሹ ውቤ የሚባሉ ሰውዩ በሞተ በዓመቱ የገጠሙት ።

ያችስ ላም ምን አለች
ወተት ታጠጣለች ቅቤ ታበላለች
በሬ ትወልዳለች ።
እረ የዚያችስ ላም ከቶ አነሳት ዋጋ
አምና አረዷት አሉ ለማይጠቀመው ሥጋ ።

### ካህን ገደል ገብቶ ስለሞተ ፥

አያችሁት ወይ የእግዜርን በደል
ያ ደብተራ ከልካይ ተምሮ ገደል ።

### እቴጌ ጣይቱ በሞቱ ጊዜ አንድ ባላገር የገጠመው ፥

በስተ ጕግሣም በኩል ሳሳብኝ ሌማቱ
በስተ ወሌም በኩል ሳሳብኝ ሌማቱ
በስተ አመዴም በኩል ሳሳብኝ ሌማቱ
ጠፍታለች መሰለኝ እንጀራ ጣይቱ ።
ሰባት ደጃዝማች ስምንተኛው ዋግ ሹም ዘጠነኛው
ራስ አንድ ጊዜ ቢመጡ
ተቀምጠ ዐያቸው አመዴ ረመጡ ።
እንደዚህ ጢሼ ጢሼ የነደድሁ እንደሆን
ያመዴ መፍሰሻው ቦታው ወዴት ይሆን ፤

### ተሠሪውን እከክ ስለዋጠው የባላገር ምሽት የገጠመችው ፥

ይዟችሁ የመጣ የቱ ነው ጌታው
ጨርሶ መንጣሪ የሰገራት ሰው ።

### ከዐድዋ ጦርነት መልስ ለዋግ ሹም ብሩ ጓንጕል የተሰጠ፤(አለቃ ሣህሉ ፥)

### መ ወ ድ ስ ።

፩ አመ ወድቁ ሕዝብ መድፍና ወጨፎ ፥
በቅድመ ሙሴ ሀብትህ ብርሃነ መለኮት ዐይተው
አርዕድ አንቀጥቅጥ ይብሉከ ዘነጸሩከ እደው
ወመተረ ምህራመ ክሣዱ ለጋላ ሕስው ።
ኢዮሰያስ ጕራዴከ ፥
በቅድመ ምኒልክ አምላክ እልፍ የሚሠዋው ።
አምነሂ ሃይማኖተከ መኰንነ ጣልያ ዕልው
ካህናተ እሳት አሽከሮችህ ሲያጠምቁት ጊዜ ደግሞው ደግመው
ወይቤ የዐቢ እምአድባረ ነገሥት አበው
ቤተ ክርስቲያን ጓንጉል ብሩ ንጉሠ ነገሥት የተከለው ።
፪ ዋግ ሹም ጓንጉል ብሩ መጽሐፍ ቀለምህ ያማረ
ይገኝብሃል ምሥጢር ለደገመህ ሁሉ ደብተራ
በምድረ ትግሬ ስፍሀት እግር ተፈረስ ሲዘራ

አሰመጠች ግብጻዌ ጠበንጃህ ኤርትራ
አግዳጅ ነውና እጅግ ሳይፈራ
ገጽከ ሎጥ ማዕከ ጥይት ገሞራ ።
ተበሃሉሂ አሽከሮችህ ዳኛው ቢያቆማቸው በግራ
መኑ ጸውያሙ ለባርቅ ወዲቦራ
አጠጣቸው አሉ መርከብ አቡስንት አረቂ መከራ
ቅድመ በወጨፎ ወድኅረ በውጅግራ ።

## መሪ ጌታ ወልደ ትንሣኤ ።

አምላከ ኤርምያስ ላህ ዘይገለብበ
በደመናሁ ግሩም ለገጸ ዮሴፍ ሰማይ
ወዘያስተዴሉ ከርመ ለገጸ ሰሎሜ ዐባይ
ዘይጠፍር ጽርሖ በዘዳኖስ ማይ
ወዐይነ ድንግል ተነ ጊሜ
ዘየዐቍር ማየ አምጣነ ውእቱ ቀዳማይ ።
ፓክስርሂ አስቆሮታዊ እንተ ልቡናሁ ጊጉይ
በስዒም ያገብኦ ለእግረ ማርያም አዶናይ
አኮኑ አይሁድ አዕባነ አሐቲ ቀላይ
አበጥዎ በጥብጣቤ ወገልበብዎ በሥቃይ

## መሪ ጌታ ሞገስ ታደሰ (ዋሮ ሚካኤል) ።

ቈስጠንጢኖስ ከርም እለዘገበሙ
ባስልዮስ ጠል ወበረድ ጎርጎርዮስ
አውገዝዎ ቃለ ወአሥርዎ በየብስ
ለዘወፅአ አማዑተ ከርሡ አርዮስ በለስ
ወልሳነ ዐይን ሰባልዮስ
ዘኢአምነ ወፅአ መጠነ ስገረ ቶማስ ወሉቃስ ።
በአፍሂ ይክህዶ ለዘየአምኖ ክርስቶስ
ጴጥሮስ ወይነ ጋዲ ዘያፈርሆ ቍረ ነፋስ
ራምኖንሰ ትጸንዕ ወኢትትከወስ
ልምላሜ ሃይማኖቶሙ ለሚናስ ወኪሮስ ።

## መሪ ጌታ ገበየሁ ።

ሠረገላ ንግሡ ለባርቅ ሠረገላሆሙ
ለኬነውተ ሕንፃ ዘዳቤር ዮፍታሔ ወሶምሶን

ሠረገላቲሃ ለሳሌም ሀገረ ዘቡር ምእመን
ለዛብሎን ሠረገላሁ
ለአድኖን ሠረገላ ንግሡ እንተ ኤፍሬም ዐይን
ሠረገላ ይእቲ ኬልቄዶን
ሠረገላሁ ለሄኖክ ዘትረውጽ በአማን
ሠረገላ ጴጥሮስ ወጳውሊ ኀለፍተ ግዮን
ሠለገላ ኤፍሬም ወምናሴ ሠረገላ ዘውራ ለገባዖን
ሐዊረ ሖረ ወፈተውዋ ሄራን
አምጣነ ከደነ ሰማያተ ከመ ሠረገላ ዘባቢሎን ።
　　ስለምንሽ ማር ነው ቅኔሽ የወይን ጠጅ
ሁሉም ይወቅልሽ አስተምሪው እንጅ
በቅኔ ጉዳናሽ ጥሩው ሠረገላ
ወደ ዕውቀት ከተማ ያደርሳል በተድላ ።
እንደዚህ ከሆነ እናቴ ሙያሽ
እስኪ ስሚ አንድ ጊዜ መወድስ ልስጥሽ ።

## መ ወ ድ ስ ፤

ሀገረ ወሎ እምነ ገጽሽ የሚያበራ
ተጭነው ደረሱ ዛሬስ በማድነቅ ሠረገላ
ከመላው ዓለም ሕዝብ አንቺን ሊጎበኙ በሞላ
በጣም ታምሪያለሽና
ለብሰሽ ለሰው ስትታይ ውበትሽን ቀጸላ
ይላልም ያየሽ ሁላ
ዐይቼ አላውቅም መቸም እንዳንች ያለ ሳዱላ ።
ገጽሽሂ የሚያስጎመጅው በውበት ደምሽ ሲቀላ
ላየው ሰው በቅርብ ሁኖ ይመስላልና ሎንባ ሾላ
አድርጎ ፍትፍት ሁሉን ሳያላምጡት ሚበላ
አከናንበው መወድስን ደቀ መዝሙርሽ ሊቀ ዋድላ ።